# የኢትዮጵያ ሕዝብ ያለፈው ቅዳሜ እና እሑድ

# ውኃ ቢያጣ ሽንት ጠጣ!

የኢትዮጵያ ሕዝብ እንዴት አንጀቴን በላው፣ እንዴት አሳዘነኝ መሰላቹህ!!!

አየ አንተ መከረኛ አሳረኛ ሕዝብ ከቶ እንዴት አባቴ ላድርግህ???

በደርግ ውድቀት ማግስት ሸአቢያ ከባሕረ ምድር (ከኤርትራ) ከተበተነው ሠራዊት ዕድለኛ የሆኑቱና ከግፍ ግድያ የተረፉቱ ሳምንታት በወሰደ የእግር ጉዞ ባዶ እጃቸውን ያለምግብና ውኃ በረሀውን አቋርጠው እንዲወጡ ሲደረግ ውኃ እንኳ ቢለምኑም የሚሰጣቸው አጥተው በውኃ ጥም ላለመሞት ሽንት ለመጠጣት ተገደው አንዱ የሌላውን ሽንት እየጠጡ ነፍሳቸውን ለማቆየት ይሞክሩ ነበረ፡፡

የኢትዮጵያ ሕዝብ ላለበት ኃይለኛ የፍትሕ፣ የዲሞክራሲ (የመስፍነ ሕዝብ) ፣ የነጻነት ውኃ ጥም ንጹሕና የጠራ የፍትሕ፣ የዲሞክራሲ (የመስፍነ ሕዝብ)፣ የነጻነት ውኃ ቢያጣና አንቀልቃይ ጥማቱ ሊገለው ነፍሱን ሊያወጣው ቢደርስ ንጹሕ የፍትሕ፣ የዲሞክራሲ (የመስፍነ ሕዝብ)፣ የነጻነት ውኃ ያልሆነ ግን የፍትሕ፣ የዲሞክራሲ (የመስፍነ ሕዝብ)፣ የነጻነት ውኃ የሚመስል ግን ያልሆነ ነፍሱንም ለማቆየት የማይረዳውን፣ ቢጎዳው እንጅ ለምንም ነገር የማይጠቅመውን ውኃ መሳይ ፈሳሽ ወይም ሽንት ፈሳሽ ሆኖ ውኃ መስሎ ስላገኘው ብቻ በጥማቱ አስገዳጅነት መጠጣቱን በሁለቱ ቀናት ሰልፎች ዓይተናል፡፡ ይሄ አያሳዝንም???

አያስለቅስም???

እዚህ ላይ ግን መነሣት ያለበት ጉዳይ ያለ ይመስለኛል፡፡ ሰልፎቹ ለዐቢይ ድጋፍ ለመስጠት ተብለው ተጠሩ እንጅ ሕዝቡ ያስተላለፈው መልእክት፣ ያስተጋባው ጥያቄ፣ ያከናወነው ክንው ሁሉ ዐቢይን የመደገፍ የማመስገን ሳይሆን ዐቢይን "የምታወራው ነገር ሁሉ እውነት ከልብህ ከሆነ ይሄን ይሄን ይሄን ጥያቄያችንን መልስ፣ ፍታ፣ ፈጽም፣ አከናውን!" የሚል ሆኖ ነው የተገኘው፡፡

ሕዝቡ ለ 27 ዓመታት ሲፈጸምበት የነበረውን አረመኔያዊና ኢሰብአዊ ግፍ የመተንፈሻ መድረክ አድርጎ ነው ኢጋጣሚውን የተጠቀመበት፡፡ ከሕዝቡ ከፊሉ ወያኔ ከ 21 ዓመት፣ ከ 23 ዓመት፣ ከ 24 ዓመት በፊት በሰፊው በወሰደው አፍኖ ወስዶ የመሠወር የማጥፋት እርምጃ የጠፉ የተሰወሩ ዜጎችን የየቤተሰብ አባላቶቻቸው ፎቶ ፎቶዋቸውን (ምሥለ አካላቸውን) ይዞ አገዛዙ ሕገወጥ በሆነ መንገድ የሰወራቸውን ልጆቹን ከሰወረበት እንዲያመጣ የሚጠይቅ ነው የነበረው፡፡ ከፊሉም የተፈጸመበትን አረመኔያዊ ግፍ በማስተጋባት ፍትሕ እንዲሰጠው የሚጮህ ነው የነበረው፡፡ ከፊሉም የወያኔ/ዐቢይን ሕገመንግሥት የተለያዩ አንቀጾች እየጠቀሰ ሲያወግዝ፣ ሲነቅፍ፣ ሲተች ነው የነበረው፡፡

የቅጥረኞቹና የከሀዲዎቹ የእነ ኢሳት፣ የነ ካሳሁን ገርማሜ ልጅና የሌሎች ታዋቂ ሰዎች እንዲሁም የወያኔ/ኢሕአዴግ ፍላጎትና ሕልም ግን ይሄ አልነበረም፡፡ የነሱ ፍላጎት የነበረው ሕዝቡ ተሰብስቦ ዐቢይን አምልኮ፣ አመስግኖ፣ ደግፎ እንዲመለስና በዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ ዘንድ የወያኔ ወንጀለኛ ባለሥልጣናት የታጎሩበት የዐቢይ አሥተዳደር የሞቀ ሕዝባዊ ድጋፍ ያለው ተደርጎ እንዲታይና አገዛዙ ከሕዝብ ጋር እርቅ ያወረደ የተስማማ መስሎ እንዲታይ፤ እንዲህ ዓይነት ግንዛቤ ከተያዘለት ከተወሰደለት በኋላም ከሕዝብ ጋር በፈጠረው ችግር ምክንያት በምዕራባውያኑ የተወሰዱበትን

እርምጃዎች የተሰጠውን ሁሉን አቀፍ የሽግግር መንግሥት ምሥረታ ትዕዛዝ "ከሕዝብ ጋር ሰላም እርቅ ፈጥሬያለሁ ማረጋገጫውም ይሄው ሕዝቡ በነቂስ ወጥቶ የጋለ ድጋፉን ሰጥቶኛል!" ብሎ ለማስነሣት ነበረ ፍላጎታቸው የነበረው፡፡

ሌላም ዓላማ አለው፡፡ እሱም አገዛዙ እንዲህ እንዲህ እያደረገ እያጃጃለ እስከ ምርጫው ከቆየ በኋላ "ወያኔ/ኢሕአዴግን ምረጡና ዐቢይ በቂ ጊዜ አግኝቶ የጀመራቸውን አመርቂ ሥራዎች መፈጸም እንዲችል ዕድሉን ስጡን?" ብሎ ለመደለል እንዲመቻቸው ነው ከወዲሁ ሕዝቡን የማግባባት ልቡንና አመኔታውን የመያዝ የመስረቅ ሥራ ነው እየተሠራ ያለው፡፡ በተደጋጋሚ በጽሑፎቸ ላይ እንደነገርኳቹህ ወያኔ ዐቢይን መግደል የሚፈልግ እስከመምሰል ድረስ ሔዶ የዐቢይ ጠላት መስሎ እየተወነ ሕዝቡ በዐቢይ ፍቅር እንዲያብድ፣ ዐቢይን እንዲያመልክ፣ ዐቢይን አለኝታው አድርጎ እንዲያስበው እያደረገ ያለው ለዚህ ነው፡፡

ዐቢይ ባለፈው ሳምንት አዋሳ ላይ ሕዝቡን ሰብስቦ ላቀረቡት የክልልነት ጥያቄ ደላይ ንግግር ካሰማ በኋላ "..... ሁለት ዓመት መታገስ ያቅታቹሀል ወይ?" ማለቱ የሚጠቁመው ሃቅ ዐቢይ ሕዝቡን እያጃጃለ ከምርጫው ካደረሰ በኋላ እንደዚህ ዓይነት ጥያቄዎች ለምርጫ መቀስቀሻና የሕዝብ ልብ መማረኪያ አድርጎ ለመጠቀም መዘጋጀቱን ቁልጭ አድርጎ ያሳያል፡፡ ወያኔ በመጪው ምርጫ ሰሞን እንደለመደው የሚያደርገውንና የማያደርገውን ነገር "አደርጋለሁ!" እያለ በዐቢይ አንደበት አጣፍጦ በማስነገር ከቻለ ሕዝቡን "እንዲህ የሚያደርጉ ከሆነማ እኛ ከመንግሥት መለዋወጡ ምን አለን? እራሳቸው ይቀጥሉ!" ብሎ ወያኔ/ኢሕአዴግን እንዲመርጥ ለማድረግ ይሄ ካልተሳካ ደግሞ በለመደው መንገድ አጭበርብሮ በሥልጣን መቀጠልን አልሞ ነው ሥራው እየተሠራ ያለው፡፡ ዐቢይ "የሽግግር መንግሥት ያቋቁማል!" ምንትስ እያልክ የቁም ቅዠት የምትቃዥ ምድረ ጅል ሁሉ ተስፋ ቁረጥ፡፡ ዐቢይ በታላቅ ትጋትና የማወናበድ ብቃት እየሠራ ያለው ሥራ ወያኔ/ኢሕአዴግን ከተጠያቂነት አስመልጦ በሥልጣን እንዲቀጥል እንዲቆይ የማድረግ ሥራ ነው እየሠራ ያለው፡፡ ምድረ ቃዣታም ንቃ!!!

ወደ ሰልፎቹ ስንመለስ ውጤቱ እንደታሰበው ባይሆንም ሰልፎቹ ይሄንን ያህል ሕዝብ አሳትፈው ይከናወኑ ዘንድ ከእስር የተፈቱ የኦነግና የግንቦት 7 አባላት የሰልፉ አዘጋጅ በመሆን የሠሩት ሥራ፣ ኢሳትም በባለቤትነት ስሜት ያደረገው ከፍተኛ ቅስቀሳ የአንበሳውን ድርሻ ይይዛሉ፡፡ የኦኤምኤን ድርሻም የሚናቅ አይደለም፡፡ ይሄንን ሰልፍ ኢሳት ጉዳዩን በባለቤትነት ይዞ ከፍተኛ የድጋፍ ቅስቀሳ ባያደርግ ኖሮ አይደለም በክፍላተ ሀገር በአዲስ አበባም እንኳ ሰልፉ ጨርሶ አይካሔድ እንደነበረ በእርግጠኝነት መናገር እችላለሁ፡፡

አሁን አደጋው ኢሳት፣ ኦኤምኤን፣ የኦነግና የግንቦት 7 አባላት ይሄንን የያዙትን እንቅስቃሴ አጠናክረው የሚቀጥሉ መሆናቸው ነው፡፡ ኢሳት ለአማራ በደልና አረመኔያዊ ግፍ "የዝሆን ጆሮ ይስጠኝ!" ብሎ ለመዘገብ ዳተኝነቱን ያሳየንና በሚያፍንበት ጊዜ እንዲሁም ግለሰቦችን እየጋበዘ ሞያዊ መርሕንና ሚዛናዊነትን ባልጠበቀ አቀራረብ አማራን ማዘለፍ፣ ታሪክን መስቆንጸል ማስጠልሸትን ሥራየ ብሎ ከተያያዘበት ጊዜ ጀምሬ የቴሌቪዥንና የራዲዮ (የምርዓየ ኩነትንና የነጋሪተ ወግን) የብዙኃን መገናኛ አገለግሎት ለአማራ ሕዝብ ያለውን ወሳኝነት አበክሬ በማሳሰብ አማራ እንደምንም ብሎ እንደ ኢሳትና ኦኤምኤን ያለ የራሱን ራዲዮና ቴሌቪዥን እንዲያቋቁም አጥብቄ ሳሳስብና ስወተውት እንደነበር ይታወሳል፡፡

ይሄንን አድርገን ቢሆን ኖሮ ዛሬ የከሀዲው ግንቦት 7 አባላትና ልሳኑ ኢሳት እንዲህ ባልተጫወቱብን ባልቀለዱብን ነበር፡፡ ይሄ አይግረማቹህ ለማየት ያብቃቹህ ገና በነፍስ በሥጋችን ይጫወቱብናል ይቀልዱብናል፡፡ እያንዳንድሽ የወያኔ፣ የሽአቢያ፣ የኦነግ፣ የግ7 ጥምረት ለአማራ ሕዝብ መልካም ዜና ይዞ የመጣ ከመሰለሽ ባትፈጠሪ ይሻልሻል፡፡ ወያኔ ምን ያህል እንዳቃተን እያያቹህ ሽአቢያን ኦነግን ጨምሮ ሲመጣ ነገሮች ምን ያህል ሊከብዱብን እጅግ ሊወሳሰቡብን እንደሚችሉ መገመት የሚሳነው ካለ ማሰብ የተሳነው መሆኑን እርግጠኛ ይሁን!!!

ኧረ ተው ወገኖቸ እስከመቸ ነው እንቅልፉ???

እስከመቸ ነው መደንዘዙ???

እስከመቸ ነው መፍዘዙ???

ከመሸ ነቅተህ ከፈርሱ መጓጎር ነው ወይ የምንፈልገው???

ይሄ ሁሉ አረመኔያዊ ግፍ፣ ይሄ ሁሉ ሰይጣናዊ ሽፍጥ ያላነቃህ ምኑና የቱስ ነው የሚያነቃህ ወገኔ???

ኧረ እናንተንስ አፈሩን ባስበላቹህ ወዲያ!!!

እስኪ የጠላቶቻችንን ቁርጠኝነት፣ እልህ፣ ትጋት፣ ጥንካሬና የሽፍጥ፣ የሴራ፣ የደባ፣ የአሻጥር፣ የክፋት ብቃትንና ዕኩይነትን ..... ተመልከቱ???

እንዲህ አዝግመህና ተኝተህ ነው እንዴ ታዲህ ይሄንን ሁሉ ፈተና የምትቋቋመው የምትወጣው???

ቆይ ያንተን የቤት ሥራ ማን የሚሠራልህ፣ ላንተ ሕይዎት ማን ዋጋ ከፍሎ ነጻ የሚያወጣህ ሰላምህን የሚሰጥህ መስሎህ ነው ተጋድመህ የምታንኮራፋው???

ከገንዘብህ፣ ከጉልበትህ፣ ከጊዜህና ካለህ ነገር ሁሉ ቅንጣትም ታክል ሳትነካብህ ሥራው በራሱ ጊዜ ተከናውኖ እንድታገኘው ነው እንዴ የምትፈልገውና የምትጠብቀው ምድረ ደነዝ???

ኧረ ተው! ተው ንቁ! አሳርራቹህ አቃጥላቹህ ገደላቹህኝ እኮ!!!

ድል ለአማራ ሕዝብ!!! ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር!!!

ሠዓሊ አምሳሉ ገ/ኪዳን አርጋው

amsalugkidan@gmail.com